## አጋርነቱ እንዴት ይተገበራል...

### 2. ውጫዊ አሠራር (የደንበኞች/ዲጂታል)

- **የባንክ መተግበሪያዎች እና USSD፦** በሞባይል ባንኪንግ መተግበሪያዎች ላይ "አንድ ሲኒ ቡና ይለግሱ" የሚል ቁልፍ ማካተት።
- **የኤቲኤም እና የቆጣሪ ዘመቻዎች፦** ደንበኞች አገልግሎት በሚያገኙበት ወቅት ተጨማሪ የዲጂታል መልዕክቶችን ማሳየት።

## የእኛ ቃልኪዳን

በዚህ ዘመቻ የሚሰበሰበው ገንዘብ 100% ሙሉ በሙሉ ልዩ እንክብካቤ ለሚፈልጉ ሕፃናት እና ለእናቶቻቸው የማቆያ ዴኬር  እንደማንኛውም ህፃናት ወለው የትራፒ አገልግሎት የሚያገኙበት፣ አልሚ ምግብ፣ ወላጆች ከሩቅ ሰለሚመጡ ለወላጆች ልጆቻቸውን ማመላለሻ ለትራንሰፓርት የሚሆን እና አቅም ማሳደጊያ ላይ ይውላል።

## ቀጣይ እርምጃዎች

ይህንን ዘመቻ ከተቋምዎ ግቦች ጋር በሚስማማ መልኩ እንዴት ማዘጋጀት እንደምንችል ለመወያየት ከድርጅትዎ የማኅበራዊ ኃላፊነት (CSR) ወይም የገበያ ጥናት (Marketing) ቡድን ጋር ለመገናኘት ሙሉ በሙሉ ዝግጁ ነን።

> "አነስተኛ ለውጥ ታላቅ መሻሻል ሊፈጥር ይችላል።"


**ያግኙን**

+251 961 23 73 67
Sabrina Orgino (Founder)
ጆይ ፉል ላይፍ (Joyful Life)
joyfullife-ethiopia.org


ቴሌብር telebirr

Telebirr Account
(Joyful Life)

**0978584800**

SOCIAL MEDIA

joyful.life.et | Joyful Life | joyethiopia | joyful.life.et




Joyfull life
Love is the key that opens the door of hope so that life may once again be joyfull.

# አንድ ሲኒ ለበጎነት

## የዕለት ተዕለት ልማድን ሕይወትን ወደሚለውጥ ድጋፍ መቀየር



**አቅራቢ:-** ጆይ ፉል ላይፍ የበጎ አድራጎት ድርጅት
**አጋሮች:-** የፋይናንስ ተቋማት እና ኩባንያዎች
**የጊዜ ሰሌዳ:-** ከ2026 ዓ.ም. ጀምሮ — የቀጠለ

# መግቢያ

## የ20 ዓመታት የቁርጠኝነት ጉዞ

ጆይ ፉል ላይፍ (Joyful Life) የበጎ አድራጎት ድርጅት ላለፉት ሁለት አስርት ዓመታት በኢትዮጵያ ውስጥ ተጋላጭ የሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ለመደገፍ በትጋት ሲሠራ የቆየ የተስፋ ብርሃን ነው።

ዛሬ፤ የእርስዎ የተከበረ ተቋም ከፍተኛ ተሳትፎ የሚጠይቅ እና ለማበርከት እጅግ ቀላል በሆነው የገቢ ማሰባሰቢያ ንቅናቄዎቻችን ላይ አጋር እንዲሆን በአክብሮት እንጋብዛለን።

የድርጅትዎን ሠራተኞች እና ደንበኞች ለአንድ ቀን፣ ለአንድ ሳምንት ወይም ለአንድ ወር ለቡና እና ሻይ መጠጫ የሚያወጡትን ወጪ እንዲለግሱ በማስተባበር፤ ልዩ እንክብካቤ ለሚፈልጉ ሕፃናት እና ለእናትየው አስተማማኝ እና ሕይወትን የሚቀይር ቀጣይነት ያለው ድጋፍ በጋራ ማበርከት እንችላለን።

# ተግዳሮቶች እና ዓላማችን

## የገጠሙን ተግዳሮቶች

ልዩ እንክብካቤ የሚሻን ሕፃን ማሳደግ ከፍተኛ ስሜታዊ፣ አካላዊ እና ፋይናንሳዊ ጥንካሬ ይጠይቃል። በሀገራችን ኢትዮጵያ በርካታ እናቶች ለልዩ ፈላጎት ላለባቸው ህፃናት የማቆያ ባታ ( ደኬር ) ፣ ለፊዚዮቴራፒ (የአካል ብቃት እንቅስቃሴ) እና ለተሟላ የአመጋገብ ሥርዓት የሚሆን አቅም በማጣታቸው ይህንን ከባድ ጉዞ ብቻቸውን ለመጓዝ ይገደዳሉ።

## የእኛ ዓላማ

ጆይ ፉል ላይፍ ይህንን ክፍተት ለመሙላት ከ20 ዓመታት በላይ ሠርቷል። ዓላማችን ግልጽ እና ቀላል ነው፦ ማንኛዋም እናት ይህንን መንገድ ብቻዋን እንዳትጓዝ ማድረግ እና እያንዳንዱ ልዩ እንክብካቤ የሚፈልግ ሕፃን የሚገባውን ክብር እና እንክብካቤ እንዲያገኝ ማስቻል ነው።

# ፅንሰ-ሐሳብ

### “ አነስተኛ ልገሳ፤ ታላቅ ተፅዕኖ ”

የገቢ ማሰባሰቢያ ስትራቴጂያችን የኢትዮጵያን የበለጸገ የዕለት ተዕለት የቡና እና የሻይ ባህል መሠረት ያደረገ ነው። ግለሰቦች ለመጠጥ የሚያወጡትን ወጪ ለሌላ ዓላማ እንዲያውሉት ጥሪ እናቀርባለን፦

**የ1 ቀን የቡና ወጪ**

ለሕፃኑ አስቸኳይ የአልሚ ምግብ አቅርቦት ይውላል።

**የ1 ሳምንት የቡና ወጪ**

ለሕፃኑ ወሳኝ የሆኑ የማቆያ ዴኬር/የማገገሚያ (Therapy) ክፍለ-ጊዜዎችን ይሸፍናል።

**የ1 ወር የቡና ወጪ**

እናቶች ልጆቻቸውን ለመንከባከብ የሚያስችላቸውን ግብዓቶች እና የማቆያ ዴኬር ድጋፎች በማቅረብ አቅማቸውን ይገነባል።

# አጋርነቱ እንዴት ይተገበራል?

## 1. ውስጣዊ አሠራር (የተቋማት/የሠራተኞች)

- **ከደመወዝ የሚቆረጥ አነስተኛ ልገሳ:-** ሠራተኞች በፈቃደኝነት በየሳምንቱ ወይም በየወሩ ከቡና በጀታቸው ጋር እኩል መጠን በቀጥታ ማበርከት ይችላሉ።
- **የተቋማት እኩል መዋጮ (Corporate Matching):-** ተቋሙ በተሰበሰበው ጠቅላላ መጠን ልክ እራሱም በመጨመር ማኅበራዊ ተፅዕኖውን እጥፍ ያደርጋል።